በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣
ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## ከጁላይ 1-10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እንዲሁም

## ከጁላይ 11-20 እና ከጁላይ 21-31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ጁላይ 2024

አዲስ አበባ

ስልክ+251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

**ርዕስ** **ገፅ**


እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ ... - 1 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ... - 2 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት ... - 2 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ... - 3 -

እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ... - 3 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ... - 4 -

እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ... - 4 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ... - 5 -

እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ... - 5 -

ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከጁላይ 11-20, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ... - 6 -

ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከጁላይ 11-20, 2024 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን ... - 6 -

እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ... - 7 -

ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከጁላይ 21-31፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ... - 7 -

እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ... - 8 -

እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውኃው በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ... - 9 -




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-871 ኢሜይል፡ emi@ethiomet.gov.et ዌብሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት አስር ቀናት ለክረምት ዝናብ መፈጠር አመቺ ሁኔታን የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ተጠናክረው ተስተውለዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው ጣቢያዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል በሀዋሳ 39.0፣ በድሬዳዋ 36.2፣ በጎንደር 33.9፣ በቢሾፍቱ 42.5 እና 41.5፣ በጎሬ 47.7፣ በጅማ 59.6 እና 33.7፣ በአዲግራት 43.7፣ በአለም ከተማ 43.0፣ በአምባ ማርያም 42.4፣ 32.2 እና 36.4፣ በደብረብርሃን 43.6፣ በሀረር 40.0፣ በላሬ 78.0፣ በላይበር 54.7፣ በጽጽቃ 46.2፣ በወላይታ ሶዶ 44.1፣ በባቱ 74.0፣ በቁልቢ 42.6 እና 36.8 በላንጌ 68.5 በአደሌ 31.0፣ በአርሲ ሮቤ 35.2፣ በአፅቢ 34.0፣ በቡለን 38.5፣ በጨፋ 34.2፣ በደብረ ታቦር 31.9፣ በጋምቤላ 35.7፣ በጋቲራ 39.4፣ በጉንዶ መስቀል 36.2፣ በእምድብር 30.2፣ በጅግጅጋ 35.5፣ በሊሙገነት 35.0፣ በማጂ 35.6፣ በነጆ 30.7፣ በፍሬወይኒ 39.5፣ በሽሬ 38.0፣ በሾላ ገበያ 32.6፣ በቴፒ 36.7፣ በወረኢሉ 30.8፣ በየትኖራ 36.6፣ በኮምቦልቻ (ሐረሪ) 38.2 እና 32.6፣ በማጀቴ 40.9፣ በቻግኒ 33.6 በአይከል 37.5 እንዲሁም በካራሚሌ 30.5 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡


ባለፉት ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የመካከለኛው፣ የምስራቅና የደቡብ ትግራይ ዞኖች፣ ከአማራ ክልል የምዕራብ፣ ማዕከላዊ እና ደቡብ ጎንደር፣ አዊ፣ ምስራቅ፣ ደቡብና እና ምዕራብ ጎጃም፣ ዋግህምራ እንዲሁም ሰሜንና ደቡብ ወሎ ዞኖች፣ የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፣ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የመተከል፣ የአሶሳ፣ የካማሺ እና የማኦኮሞ ልዩ ዞን፣ ከጋምቤላ ክልል መዠንግ፣ አኝዋክ፣ ኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ዞን ዞኖች፣ ከኦሮሚያ ክልል ቄሌም ወለጋ፣ ምዕራብና ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮጉዱሩ፣ ኢሉባቡር፣ ጂማ፣ ቡኖ በደሌ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ቦረና፣ ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ምስራቅ ሸዋ ዞኖች፣ አዲስ አበባ፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ሸካ፣ ኮንታ፣ ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ እና ከፋ ዞኖች፣ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀላባ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ጠምባሮ፣ የየም ልዩ ዞን፣ ከሱማሌ ክልል የፋፋን ዞንና የሲቲ፣ ዞኖች፣ ከአፋር ክልል ዞን ቅልበቲ፣ፈንቲ፣ሀሪ እና ጋቢ፣ እንዲሁም ድሬዳዋና ሀረሪ ላይ ከ30-264 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ5-9 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ ከኦሮሚያ ክልል፣ የባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ ዞን፣ ጋሞ፣ ጌዲኦ፣ ጎፋ፣ ደቡብ ኦሞ፣




ስልክ+251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ባስኬቶ ዞኖች ላይ ከ6-30 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ 1-4 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲወዳደር ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፤የመካከለኛው፣ የምስራቅና የደቡብ ትግራይ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የምዕራብ፣ ማዕከላዊ እና ደቡብ ጎንደር፣ አዊ፣ ምስራቅ፣ ደቡብና እና ምዕራብ ጎጃም፣ ዋግህምራ እንዲሁም ሰሜንና ደቡብ ወሎ ዞኖች፤ የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የመተከል፣ የአሶሳ፣ የካማሺ እና የማኦኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል መዠንግ፣ አኝዋክ፣ ኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ዞን ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል ቄሌም ወለጋ፣ ምዕራብና ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮጉዱሩ፣ ኢሉባቡር፣ ጅማ፣ ቡኖ በደሌ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ቦረና፣ ሰሜን ሸዋ(ሰላሌ)፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ምስራቅ ሸዋ ዞኖች፣ ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ፤ ከአፋር ክልል ዞን 1፣ 2፣ 3፣ 4 እና 5፤ የሲዳማ ክልል ዞን፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀላባ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ጠምባሮ የየም ልዩ ዞን፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ ዞን፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ሸካ፣ ኮንታ፣ ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ እና ከፋ ዞኖች እንዲሁም አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋና ሀረሪ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን አግኝተዋል (ካርታ 3)፡፡





ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2024 ድረስ ዝናብ የዘነባባቸዉ ቀናት



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-871 ኢሜይል፡ emi@ethiomet.gov.et ዌብሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረዉ
የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር


## እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አስር ቀናት በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚና የመኸር ሰብል አብቃይ አካባቢዎች ላይ ብዙ ቦታዎችን ያዳረሰ እርጥበት እንደነበራቸው የተሰበሰቡና የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ይህም የተገኘው እርጥበት ከጁላይ ጀምሮ ለሚዘሩ የተለያዩ የመካከለኛ ጊዜ ሰብሎች ለመዝራትና በታቀደዉ መሰረት የግብርና እንቅስቃሴን ለማከናወን አመቺ ሁኔታ የነበረው ሲሆን፤ አስቀድምው ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎች የውሃ ፍላጎታቸውን ከሚሟላት አንፃር የጎላ ሚና ከመኖሩም በላይ ከኤፕሪል ጀምሮ ቀደም ብለው ለተዘሩ እንደ በቆሎና ማሽላ ለመሳሰሉ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች፤ ለተለያዩ ቋሚ ተክሎችና የጓሮ አትክልቶች በተሟላ ሁኔታ እንዲያድጉ የጎላ አስተዋፅዖ ነበረው፡፡ በተጨማሪም በአርብቶ አደርና በከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የነበረው እርጥበት የተፈጥሮም ሆነ የሰው ሰራሽ ምንጮችን ከማጎልበቱም በላይ የተሻለ የመጠጥ ውሃና የግጦሽ ሳር አቅርቦት እንዲኖር



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-871 ኢ.ሜይል፡ emi@ethiomet.gov.et ዌብሳይት www.ethiomet.gov.et

አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ በሌላም በኩል በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የነበረው ከባድ ዝናብ እንዲሁም ባሳለፍናቸው ቀናት በተከታታይ ዝናብ በማግኘት ላይ በነበሩ ቦታዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበት መብዛት እና በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ለወንዝ መሙላትና ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ላይ የጎርፍ መከሰት የነበረ ቢሆንም፤ በግብርናዉ እንቅስቃሴ ላይ ያደረሰዉ የጎላ አሉታዊ ተፅዕኖ አልነበረም፡፡ (ካርታ 4)፡፡





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አስር ቀናት የክረምት ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የእርጥበት ሁኔታው የተጠናከረ እንደነበር የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ። ከዚሁ ጋር በተያያዘም በአብዛኛው አባይ፣ ተከዜ፣ አፋር ደናክሌ፣ ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ የላይኛው እና የመካከለኛው የስምጥ ሸለቆ፣ አዋሽ፣ ዋቤ ሸበሌ እና የገናሌ ዳዋ እንዲሁም ኦጋዴን ተፋሰሶች ላይ በጣም ከፍተኛ የእርጥበት መጠን የነበራቸው ሲሆን በጥቂት የአባይና የዋቤ ሸበሌ ኪስ የተፋሰሱ አካባቢዎች ላይ እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆነ እርጥበት ነበራቸው። ይህም ሁኔታ ለገጸ ምድርም ሆነ ለከርሰ ምድር የውኃ ሀብት መሻሻል እንዲሁም የግድቦችን እና የወንዞች የውኃ አቅም ከማጎልበት አንጻር አዎንታዊ ሚና ነበረው (ካርታ 5)፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-871 ኢ.ሜይል፡ emi@ethiomet.gov.et ዌብሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በመደበኛ ሁኔታ በጁላይ ሁለተኛው አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አከባቢዎች ላይ ይበልጥ የሚጠናከሩና ሲሆንና በብዙ ስፍራዎቻቸው ላይ የተስፋፉ ዝናብ የሚያገኙበት ወቅት ነው፡፡

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ተጠናክረው ይቀጥላሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በሰሜን፣ በመካከለኛው እና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6)፡፡


በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ጅማ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ሆሮ ጉዱሩ፣ ቄለም ወለጋ፣ ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ምስራቅ ሸዋ ዞኖች፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ምስራቅና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ፤ አዲስ አበባ፤ ሀረር እና ድሬ ዳዋ፤ ከአማራ ክልል ሰሜን፣ ማዕከላዊ፣ ደቡብ እና ምዕራብ ጎንደር፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ ዋህግምራ፣ አዊ፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-871 ኢሜይል፡ emi@ethiomet.gov.et ዌብሳይት www.ethiomet.gov.et

ሰሜን ሸዋ፣ የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፤ ከትግራይ ክልል ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፤ ማዕከላዊ፣ ምስራቅ እና ደቡብ ምስራቅ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ አውሲ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ ፓዌ፤ አሶሳ፤ ካማሺ ዞኖች እና ማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ፤ ከጋምቤላ ክልል ኑዌር፣ አኙዋክ፣ ማዣንግ እና የኢታንግ ልዩ ዞን፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ሃዲያ፣ ሀላባ፣ ከምባታ፣ ስልጤ፣ የየም ዞኖች፣ ጠምባሮ፣ ቀቤና እና ማረቆ ልዩ ወረዳ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ፣ ጋሞ፣ ወላይታ፣ ጌድኦ፣ ባስኬቶ እና አማሮ ዞኖች በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም በደቡብና ምስራቅ ትግራይ፤ ምዕራብ፤ ምስራቅና ሰሜን ሸዋ፤ አዲስ አበባ፤ ደቡብ አፋር፤ ጋምቤላ፤ መተከል እና በጎንደር ዞኖች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6 እና 7)፡፡

በሌላ በኩል ከዕለት ወደ ዕለት ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት በሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ ዞኖች፤ ሀረር እና ድሬ ዳዋ፤ ከሱማሌ ክልል ሲቲ፣ ፋፋን፣ ጀራር፣ ኤረር፣ ኖጎብ፣ ሊበን እና ዳዋ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ጋቢ እና ሀሪ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንሶ፣ አሪ ደራሼ፣ ቡረጂ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6)፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከጁላይ 11-20, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ


ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከጁላይ 11-20, 2024 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-871 ኢሜይል፡ emi@ethiomet.gov.et ዌብሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በመደበኛ ሁኔታ በጁላይ ሶስተኛዉ አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ይበልጥ ይጠናከራሉ፡፡ በመሆኑም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በሰሜንና በሰሜን ምስራቅና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ብዙ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸል (ካርታ 8)፡፡




ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከጁላይ 21-31፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-871 ኢሜይል፡ emi@ethiomet.gov.et ዌብሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት የክረምት ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ ይኖተራቸዋል፡፡ ስለሆነም የሚጠበቀው እርጥበት ከጁላይ ጀምሮ የሚዘሩ የተለያዩ የመካከለኛ ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራት፤ አስቀድምው ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎች የውሃ ፍላጎታቸውን ከሟሟላት አንፃር፤ ከኤፕሪል ጀምሮ ቀደም ብለው ለተዘሩ እንደ በቆሎና ማሽላ ለመሳሰሉ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎችን እንዲሁም ለተለያዩ የቋሚ ተክሎችና የጓሮ አትክልቶች በተሟላ ሁኔታ እንዲያድጉ የውሃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንፃር ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ እንዲሁም በባለፉት ቀናት በቂ እርጥበት ባልነበራቸው አካባቢዎች የሚጠበቀው እርጥበት የሰብሎችን የውኃ ፍላጎት ከማሟላትም ሆነ የግብርና ተግባራትን ለማከናወን አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል። በተጨማሪም በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የሚጠበቀው እርጥበት የመጠጥ ውሀ አቅርቦትንም ሆነ የግጦሽ ሳር ልምላሜና የተፈጥሮም ሆነ የሰው ሰራሽ ምንጮችን ከማጎልበት አንጻር አዎንታዊ አስተዋፅዖ ይኖረዋል፡፡

በሌላ በኩል በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የሚኖረው ከባድ የዝናብ መጠን በማሳዎች ላይ የውሃ መተኛት፣ የአረም መስፋፋትና ከእርጥበት መብዛት ጋር ተያይዘው የሚከሰቱ የሰብል በሽታዎች ሊኖር ስለሚችል ተያያዥ ጉዳቶችን ለመቀነስ ብሎም ለማስቀረት የሚያስችሉ የውኃ መፋሰሻ ቦዮችን የማዘጋጀትና የጸረ አረምም ሆነ የጸረ ተባይ መከላከል ዝግጅት ከወዲሁ አስቀድሞ ማከናወን ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ የግብርና ግብዓቶችን ከመጠቀም አስቀድሞ ሊኖር የሚችለውን የዝናብ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ማከናዎን ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም ከባድ ዝናብ በሚጠበቅባቸው አንዳንድ ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑና በረባዳማ አካባቢዎች ላይ የሰብሎች በጎርፍ የመጠረግ እና የአፈር መሸርሸር ሊከሰት ስለሚችል ይህንን ለመከላከል የሚያሰችል የጎርፍ መቀልበሻ ቦዮችንና የውሃ ማንጣፈፊያ ዘዴዎችን ከወዲሁ በማዘጋጀት አስፈላጊውን የቅድመ ጥንቃቄ ስራዎች ማከናወን ያስፈልጋል፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-871 ኢ.ሜይል፡ emi@ethiomet.gov.et ዌብሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

### በውኃው በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት በአብዛኛው አባይ፣ ተከዜ፣ አዋሽ፣ ባሮአኮቦ፣ የላይኛው እና የመካከለኛው ኦሞጊቤ፣ አፋር ደናክል፣ የስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛው ዋቤ ሸበሌ እና የገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት ሁኔታ ይኖራቸዋል፡፡ ይህም ሁኔታ በተፋሰሶች ያለውን የገጸ ምድርና የከርሰ ምድር የውኃ ኃብትን ከማሻሻል እንዲሁም የግድቦችን እና የወንዞች የውኃ መጠን ከማሳደግ አንጻር አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም ለሃይል ማመንጫም ሆነ ለመስኖ ስራ የሚያስፈልግ በቂ የውሃ ክምችት እንዲኖር የሚያስችል በመሆኑ የሚመለከታቸው አካላት የዝናብ ውኃን ለማሰባሰብና ለማከማቸት የሚያስችል ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ ተፋሰሶች ላይ ሊኖር ከሚችለው ከፍተኛ የእርጥበት ሁኔታ ጋር ተያይዞ የቅጽበታዊ ጎርፍ ክስተትና የወንዝ ሙላት ሊኖር ከመቻሉ ጋር ተያይዞ፣ የጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ የከተማም ሆነ የገጠር አካባቢዎች ላይ በህይወት በንብረትም ሆነ በመሰረተ ልማት ላይ ጉዳት እንዳያስከትል የጎርፍ ማፋሰሻዎች ማፅዳት እንዲሁም ግድቦች እና የተለያዩ የውሃ ማጠራቀሚያዎችን የቅርብ ክትትል በማድረግ ስጋትን አስቀድሞ በመለየት ጉዳትን ለመቀነስ እና ብሎም ለማስቀረት የሚያስችል ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-871 ኢሜይል፡ emi@ethiomet.gov.et ዌብሳይት www.ethiomet.gov.et